Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# ጠረፋማ አካባቢዎችን ማበልጸግ? የመዋዕለ ንዋይና የማዕድን ቁፋሮ ፖለቲካ በድካሪ 2010 ኢትዮጵያ

በዮና ፄዴኪንድ

## ማጠቃለያ


- በ2012 (እ.ኤ.አ. በ2019) የብልጽግና ፓርቲ ምስረታን ለስከትሎ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የሚመራው መንግሥት የማዕከላዊ መንግሥትንና እና 'የጠረፍ አካባቢዎችን' ክልላዊ መንግሥታት ግንኙነት ለማስተካከል ወጠነ። ይህም የመዋለ ንዋይና የገቢ ክፍፍል አስተዳደር ማሻሻያዎችን ያካተተ ሲሆን፤ በተፈጥሮ ሀብቶች የበለፀጉ ግን በፖለቲካ የተገለሉ ክልሎች ፍትሐዊ 'ብልፅግናን' እንዲያገኙ ያለመ ነበር።

- የብልጽግና ፓርቲ አመራር የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ይከተለው ከነበረው መንግሥት መራሹ ልማታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመውጣትና የገበያ ነፃነትን በመተግበር፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን (ለምሳሌ፣ ስኳር ማምረቻዎችን) ወደ ግል ይዞታ ለማዘዋወር፣ በማዕድን ቁፋሮ ዘርፍ (ማለትም በወርቅ፣ በነዳጅ/ዘይት) ኢንቨስትመንቶችን ለማሳደግ እንዲሁም የአፈፃፀም ድክመት ያላቸውን ዘርፎች (ለምሳሌ ጨው፣ ስኳር) ምርታማነት ለማሻሻል ቃል ገብቷል።

- የማዕድን (የጨው/ወርቅ) ቁፋሮ ሥራ ዕድሎችን ለወጣቶች ወይም ለሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል ማስተላለፍ፣ እንዲሁም ከሚገኘው ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ በክልሎች ለማስቀረት ቃል መግባትን ጨምሮ የታቀዱት የመልሶ ክፍፍል ማሻሻያዎች፣ በአብዛኛው ፖለቲካዊ ተነሳሽነት ያላቸው ሲሆኑ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አፍ ለማስያዝና ለመንግሥት ታማኝ የሆኑ የክልል ባለሀብቶችን ለመፍጠር/ለመያዝ ያለሙ ነበሩ።

- በብልጽግና ፓርቲ የሚደገፋና በዋናነት ከኦሮሚያ እና ከአማራ ክልል የተውጣጡ ባለሀብቶች ከዚህ ቀደም በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ተባባሪዎች ወይም በመንግሥት የተያዙ ስትራቴጂካዊ የኢኮኖሚ ዘርፎችን (ለምሳሌ ወርቅ፣ ስኳር እና ጨው) ይዘዋል። ይህም የፖለቲካ ማዕከሉ የክልል አሊያም የብሔር ጥምረቱን በቀየረ ቁጥር ያሉትን የማዕድን ቁፋሮ ሀብቶች ለመቆጣጠር ያለመ ፉክክርን ቀስቅሷል።

- በብልጽግና ፓርቲ አመራር ዘመን የሚስተዋሉ አንዳንድ የኢኮኖሚ ችግሮች ስትራቴጂያዊ የማዕድን ዘርፎችን ማስተዳሳቸውን ቀጥለዋል። ዋና ዋና ሀብቶችን (ለምሳሌ ጨውና ስኳር) በሞኖፖል መያዝ፣ የማኅበረሰብ ምክክር እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አለማካሄድ፣ ዉጤታማ ያልሆኑ ፕሮጀክቶችን መሰረዝ (ለምሳሌ ዘይት/ጋዝ፣ ወርቅ) እንዲሁም በአስተዳደር ጉድለትና በምርታማነት ዕጦት ያልተሟሉ የፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች (ሀብትን ከመንግሥት ወደ ግል ይዞታ ማዛዋወር) ከችግሮቹ መካከል ይጠቀሳሉ። እነዚህ ሁኔታዎች የፓርቲውን የመጀመሪያ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ በማዳተት ወደ መጪው ሁለተኛ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ተሳልፈወዋል።

- ከማዕድን ቁፋሮ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ሁከቶች የተለመዱ ናቸው። እነዚህ ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰቱትን የድንበር እና የግዛት ግጭቶች፣ የብሔር ተኮር ጥቃቶች እንዲሁም በመንግሥት የሚመሩ ትጥቅ የማስፈታት እና የመልሶ ማቋቋም ዘመቻዎች ምክንያትነትን ያካተቱ ናቸው።

- መንግሥት አምራች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ለሰላም ግንባታ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ይናገራል። ብዙ ጊዜ ግን እንደዚህ ያሉ ፕሮጀክቶች ለሀብት ክፍፍል ውዝግቦችና ለግጭት ተጋላጭ ናቸው። ይህም በተለይ በፕሮጀክቶች ምስረታ እና አሠራር ላይ የማኅበረሰብ ምክክርን ካልተከተለ ወይም የታጠቁ ፀረ-አሸባሪዎች እና የተደራጁ ወጣቶች ፕሮጀክቶቹ የፌደራል መንግሥትን ወይም የክልል ባሀብቶችን ብቻ የሚጠቅሙ ከመሰሳቸው የሚፈጠር ይሆናል።

- የብልጽግና ፓርቲ የኢትዮጵያን የመሀል-ዳር ፖለቲካ ለማስተካከል ቃል ቢገባም፣ በክልሎች እና በፖለቲካ ማዕከሉ መካከል ያለው የኃይል ሚዛን አልተቀየረም። ይሁን እንጂ፤ ምንም እንኳን የተለያዩ ጥምረት አጋርነት መፍጠሪያ መንገዶች ቢሆኑም አዳዲስ ፖሊሲዎችን ማውጣት፣ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ስራዎችን መስራት፣ የፖለቲካ ሃይሉን ማዕከላዊ ማድረግ እንዲሁም አንዳንድ (የብሔር ትስስር ያላቸው) ባለሃቶችን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ በፓርቲው ሥር ቀጥሏል።

## የኢትዮጵያ ሰላም ምርምር ተቋም (Peace Research Facility)

ይህ ሪፖረት ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም (PRF) የተፃፈ ነው። የሰላም ምርምር ተቋም በሰላም እና በግጭት ላይ ወቅታዊ ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ለግጭት አገናዛቢ ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚሰጥ ገለልተኛ ተቋም ነው። ተቋሙ የሚተዳደረው በስምጥ ሸለቆ ጥናት ተቋም (Rift Valley Institute) ሲሆን የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በእንግሊዝ መንግሥት ነው።

*ሪፖረቱ እውቀትን ለሰላም (Knowledge for Peace (K4P)) አካል በሆነው የኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢዎች መዋዕለ ንዋይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፕሮጀክት ሥር የተፃፈ ሲሆን፤ በአሰበ ረጋሳ፣ በደመና አበበ፣ በደረጀ ፈይሳ፣ በአቡበከር ያሲን፣ በጁዌሪያ አሊ፣ በቤኔዲክት ካምስኪ እና በዮሐንስ ይትባረክ በጉዳዩ በተደረጉ አራት ጥናቶች ላይ ያጠነጥናል።*

## ስለ ጸሐፊው (The Author)

ጸሐፊው ዮና ዌዴኪንድ ከሁምቦልት ዩኒቨርስቲ በርሊን የዶክትሬት ዲግሪ ያላችወና መቀመጫውቸውን በርሊን በማድረግ በኢትዮጵያ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ምርምር የሚያደርጉ አጥኚና ተንታኝ ናቸው። የPRF/RVI አማካሪ በመሆን በሀብት እና በድንበር ዙሪያ የተሰሩ ሁለት የዕውቀት ለሰላም ፕሮጀክቶችን መርተዋል።

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility